# የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ራዕይ ፥ ተልዕኮዎችና እሴቶች

ኦክቶበር 8/2019

# ራዕይ

በወንጌል እውነት የቆመች፣ በመንፈስ ቅዱስ የምትመራ፣ አማኞች በፍቅርና በኅብረት ተያይዘው ደቀ መዝሙር አገልጋዮች የሆኑባት፣ በአውሮፓና ብሎም በዓለም ጨውና ብርሃን ሆና የጌታን አዳኝነት በሙላት የምታውጅ ቤተ ክርስቲያን ተገልጣ ማየት።

# ተልዕኮ

- ቋንቋቸውንና ባህላቸውን በመጠቀም ለሕዝቦች ሁሉ ወንጌልን በክብርና በኃይልና በስልጣን መስበክ።
- ልዩነታችንን በማቻቻል እርስ በእርሳችን በፍቅርና በሕብረት ተያይዘን የክርስቶስን እውነተኛ ፍቅር መግለጥ።
- ቤተ ክርስቲያን ያሉትንና ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡትን አማኞች በትጋት በመከታተል በክርስቶስ ትምህርት የጌታ ደቀ መዛሙርት ማድረግ።
- ደቀ መዛሙርት የሆኑትን ጸጋቸውን በመለየት ለአገልግሎት ማብቃትና ማሰማራት።

# የቀጠለ…

- በክርስቶስ ትምህርት አምነው ደቀ መዝሙር ከሆኑ ሰዎች ጋር በቃልና በሥራ የተገለጠ እውነተኛ አምልኮ ማድረግ።
- በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ውስጥ ተሳታፊ በመሆን የጽድቅንና እውነት ተጽእኖ ማምጣት።

# እሴቶች

- **የእግዚሐብሔር ቃል**፡- የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና የሚሠራ ባለ ሥልጣን እንደሆነ እንቀበላለን።
- **ፍቅር** ፡- ለእግዚአብሔርና ለሰዎች በሥራ የተገለጠ ፍቅራችንን እንገልጣለን።
- **አድነት እና ኅብረት** ፡- በአንድ አካል ውስጥ ያለን ልዩ ልዩ ብልቶች እንደመሆናችን አንድነታችንን በሰላም ማሰሪያ ለመጠበቅ እንሰራለን።
- **ትህትና** ፡- ከእኔ ይልቅ ወንድሜ የተሻለ ነው ብለን በትህትና እንቆጥራለን።
- **ታማኝነት** ፡- በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት በታማኝነት ለመመላለስ እንተጋለን።

# የቀጠለ…

- **መሰጠት፡–** አገልግሎቱ የሚጠይቀውን ዋጋ በመክፈል መሰጠታችንን እንገልጣለን።
- **ምሳሌነት፡-** ሁሌም ለሌሎች ምሳሌ ለመሆን እንጥራለን።
- **እምነት፡-** በእምነታችን ለመጽናት በጌታ ጸጋ እንበረታለን።
- **ራስን መመርመር፡-** ቆም ብለን አካሄዳችንን ለመመርመር እድል እንሰጣጣለን ስህተቶችንም ለማረም እንጥራለን።